# ያላረፉ ሰፍሶች

ደራሲ፤ ቆንጂት ብርሃን

ወፍ በረር ምልከታ

አስቀድሞ ‘ምርኮኛ’ ነበረ። እነሆ ‘ያላረፉ ነፍሶች’ ምርኮኛን ተከተለ። የደራሲ ቆንጂት ብርሃን ዳግማዊ በረከት። ስለምን የመፅሀፉ ርዕስ ‘ያላረፉ ነፍሶች’ ሆነ? አመራማሪ ነው። ኮርኳሪ ነው። ከርዕሱ ጀርባ የሚገኙትን ያላረፉ ነፍሶች ለማወቅ ያጓጓል። እኒህ ነፍሶች እነማን ናቸው? ስለምንስ ነፍስያቸው እረፍት አልባ ሆኑ? እኒህንና ተዛማጆቹን መመለስ የሚቻለው ታሪካቸውን ሲቋደሱ፤ በታሪካቸው ውስጥ ሲዋኙ ብቻ ነው - መፅሐፉን ሲያነቡ። ደራሲ ቆንጂት ደግሞ እንደ ‘ምርኮኛ’ መፅሐፍዋ እዚህም የተዋጣላት ‘ታሪክ አውጊ’ (ስቶሪ ቴለር) መሆኗን በአራት ነጥብ አስረግጣለች።

‘ያላረፉ ነፍሶች’ ሰፊ የታሪክ ዘመንን እና የታሪክ ሁነቶችን ያካተተ በአስራ አንድ ሰፋፊ ምዕራፎች ተዋቅሮ አራት መቶ ገፆች ያሉት ግዙፍ መፅሐፍ ነው። እንዲህ ያለን መፅሀፍ በጥቂት አንቀፆች ሸብቦ ማስተዋወቅ ደግሞ አዳጋች ከመሆኑም በዘለለ ጎደሎነቱ የሚያመዝን መሆኑን ከወዲሁ ማሳወቅ እንወዳለን።

ኢትዮጵያ ከ1950ዎቹ ወዲህ እስካለንበት ዘመን በቀዳማይ ዘመን ታሪኳ አይታ የማታውቀው የታሪክና የህልውና ማዕበል ውስጥ ገብታለች። በ1966 ዓ/ም የተነሳው የህዝባዊ ማዕበል መርከብ (አብዮት) እነሆ በተገቢው ጊዜና ቦታ በተገቢው ካፒቴን/መሪ ተሾፍሮ መልህቁን ሳይጥል እየተነሳና እየወደቀ እዚህ ደርሷል። ‘ያላረፉ ነፍሶች’ ታሪክ በዚህ ማዕበል ውስጥ ተሳፍሮ የነበረውን የአብዮቱን  አቀጣጣይና ባቀጣጠለው አብዮትም የነደደውን ትውልድ ታሪክ ይተርካል።

በአብዮቱ መባቻ ከፍቼ ከተማ የሚጀምረው ታሪክ ባለቤት የሆነችው ገፀባህሪ - ንፁህ - ያላረፉ ነፍሶች መዋቅር ምሶሶ ናት። በንፁህ ዙሪያ በመፅሐፉ ውስጥ የሚመጡትና የሚሄዱት ገፀ ባህሪያት ‘እልፍ’ ናቸው - የዛ ተስፈኛ ትውልድ አካላት። እኒህ ‘እልፍ’ ገፀ ባህሪያት ለአንባቢው ቅርብ ብቻ ሳይሆኑ አንባቢውንም በተለያዩ የስሜት እርከኖች ውስጥ አስገብተው የሚሰቅዙም ጭምር ናቸው። ኢሕአፓውያኑም ሆኑ ደርጋውያኑ፤ መኢሶናውያኑም ሆኑ ከኢህፓ ያፈነገጡ፤ የቀበሌ ካድሬዎቹም ሆኑ አብዮት ጠባቂያኑ፤ የመንግሥት ሠራተኞቹም ሆኑ ገበሬዎቹ፤ እናቶቹም ሆኑ የፋብሪካ ላብ አደሮቹ፤ የቀን ሠራተኞቹም ሆኑ ነጋዴዎቹ ሁሉም ‘ያላረፉ ነፍሶች’ ውስጥ ህይወት ዘርተው ፍንትው ብለው ይታያሉ። ከደራሲዋ አንጓ ክህሎት አንዱ ይህ ነውና። የታሪኩ ገፀ ባህሪያትና አንባቢ ሥንሠለታዊ ቁርኝት መፍጠር መቻላቸው፤ መናበባቸው።

የዚያ አብዮት አቀጣጣይ ትውልድ ተስፋ ነበረው። ዓላማ ነበረው። ግብ ነበረው። ኢትዮጵያን የሠላም የዴሞክራሲ የብልፅግና የህዝብ አስተዳደር የሰፈነባት እና የህዝቦቿ እኩልነት የተረጋገጠባት ታላቅ ሀገር የማድረግ። ያ የአብዮቱ አንዳጅ ትውልድ ከራሱና ከቤተሰቡ የሚያስበልጠውና የተሰዋለትም ድርጅት ነበረው። ‘ያላረፉ ነፍሶች’ የሚተርከው ስለ እኒህ በዚህ ትውልድም እንኳ ያልተጨበጡ ተስፋዎች የዚያን ወጣት ትውልድ ትግልና መሥዋዕትነት እስርና ስቅይት ተስፋ መቁረጥና ስደት ነው። ትውልዱ ራሱን አሳልፎ

የሰጠለትና ወደ ተራራው አናትም ወጥቶ ብርሃኑን በተስፋይቱ ምድር ሁሉ ይረጫል ብሎ ያመነበት ድርጅት ኢሕአፓ ዐይኑ እያየ ጆሮውም እየሰማ እንደ ጉም ሲበተንበት የደረሰበትንና ያለፈበትን ወደር አልባ ቅስም መሰበርና ሰቆቃ እንደ ፊልም በሚታይ ስዕላዊ ቋንቋ ይተርካል።

'ያላረፉ ነፍሶች' ከገፀ ባህሪያቱ ሰዋዊ ሕይወት ባሻገር የታሪክ ፍሰቱ አይጎረብጥም። አያዛጋም። በእያንዳዱ የታሪክና የድርጊት ሂደት መንዛዛት አልያም አለመያያዝ አይታይም። የትላንት ወዲያውን ታሪክ ከትላንቱ የትላንቱን ደግሞ ከዛሬ እያቆራኘ የሚወርደው ትርክት የዛሬውን ታሪክ ለነገ ለማድረግ ከትላንቱ ታሪክ ውድቀትና ብርታት መማር ግድ እንደሚልም እያዋዛ ነው ወደ ማደሪያው/ፍፃሜው የሚያዘግመው።

ከ1966 ዓ/ም መባቻ ተነስቶ እስከ 1983 ዓ/ም ባለቁምጣዎቹ አዲስ አበባን እስከተቆጣጠሩበት የዘለቀው 'ያላረፉ ነፍሶች' ታሪክ ኢትዮጵያና ወጣት የለውጥ አራማጅ ትውልዷ የተጓዙበትን ጥምዝምዝ በየጎራው የጠፋውን ህይወት በዚህ ሁሉ ስቃይ ትርምስና ጥፋት ማግሥትም እነዚያ በዛን ትውልድ የተነሱ የለውጥ ጥያቄዎች ዛሬም መልስ አልባ ሆነው በዛሬው ትውልድም የቀጠሉና አያሌ መሥዋዕትነትም እየተከፈለባቸው መሆናቸውንም በአንክሮና በሀዘን የምናይበት የታሪክ ዕውነታ መስታየታችን ሆኖ ይገኛል። ይህንን መፅሀፍ ማንበብ ያለፈው ወጣት ትውልድ የዓላማና የመስዋዕትነት ትግል ያለ ፍሬ መና ሆኖ የመቅረቱን ምክንያት መገንዘብ ብቻ ሳይሆን የዛሬውም ትውልድ ዓላማና መሥዋዕትነት ፍሬ አልባ እንዳይሆን ተሞክሮንና ዘላቂ መፍትሄንም ለማንሰላሰል ብርቱ ጉልበት ይሆናል። እንዲህ ያለውን የታሪክና የትውልድ ቅርስ አዘጋጅታ ላበረከተችልን ደራሲ ቆንጂት ብርሃን ገለታ ይግባትና!!

መስፍን ማሞ ተሰማ
ጥር 2010 ዓ/ም (ጃንዋሪ 2018)
ሲድኒ አውስትራሊያ

# ያላረፉ ነፍሶች

“ያላረፉ ነፍሶች” በአንዲት በ1960ውቹ ውስጥ በነበረች ወጣት ሕይወት ዙሪያ እያጠነጠነ የዘመኑን ዕውነታ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። እነዚያ ወጣቶች የተነሱበትን ምእራፍ፣ የሄዱበትን ጎዳና፣ የተቀበሉትን መከራ... ወላጆች፣ በተለይም እናቶች በአጠቃላይም ማኅበረሰቡ የተጎነጨውን የመከራ ጽዋ ያስነብበናል። እኒያ ወጣቶች ለሐገራቸው የነበራቸውን ምኞት፣ ምኞታቸውን ለማሳካት የፈጸሙትን ተግባር፣ ከተቃወሙት ሥርዓት የወረደባቸውን በትርና በድርጅታቸው ውስጥ የተፈጠረው መከፋፈል ያስከተለባቸውን ጉዳት... ይነግረናል።

የሆነው ሁሉ ሆኖ ቢያልፍም፤ ከፊሉ ሞተው፣ የተረፉትም በሕይወት የመቆየት ዕድል ቢገጥማቸውም፤ እንደሰው ለመኖር ጥረት ቢያደርጉም... ለማረፍ ያልታደሉ ነፍሶቻቸው ግን እንደዋተቱ መኖራቸውን ያመላክተናል። መጽሐፉ፤ ባለታሪኳ ከልጅነት እስከወላጅነት ዕድሜ ያሳለፈችውን የሕይወት ውጣ ውረድ በእውነተኛ ታሪክ ላይ ተመርኩዞ፣ በልብ ወለድ የአጻጻፍ ስልት ያቀርብልናል።

**ከመጽሐፉ የተወሰዱ፡**

...መንግሥት ቢገድልና ቢያስር፣ የሆነ ያልሆነ ውንጀላ ቢደረድር ሰሚ ጆሮ አላገኘም። ሁለንተናቸውን ለሕዝቡ የሰጡ ትንታግ የሆኑ የኢሕአፓ ልጆችና፣ የተባ ብእር ሕዝቡ እንዳይፈራና እንዳይታለል እያነቁት ከኢሕአፓ ጎን እንዲሰለፍ ጥረታቸውን ቀጥለዋል። ሳሩ ቅጠሉ፣ አጥሩና መንገዱ... ሁሉም ለኢሕአፓ ድጋፉን የሚሰጥ ይመስላል። “የሕዝብ ጥያቄ እስኪመለስ ድረስ ትግላችን ይቀጥላል” አለች ንጹሕ ለራሷ።

-------------------------

...ሰነዱ በኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ውስጥ ስለተፈጠረው መከፋፈል የሚናገር መርዶ ነጋሪ ጽሑፍ ነበር፡፡ ፀጥ ባለው ሌሊት ውስጥ የንጹሕ ልብ ብቻ ትደልቃለች፤ በክፍሉ ውስጥ ሌላ ሰው ቢኖር የልቧ ምት ሊረብሽ እንደሚችል እስከምታስብ ድረስ!  ማንበቧን ግን ቀጠለች፡፡ ልቧ በአፏ በኩል ዘላ ለመውጣት ስትታገል ይሰማታል፡፡ ቢሆንም ማንበቧን ልታስቆማት አልቻለችም፡፡ ገፆቹን አንድ በአንድ ገለጠቻቸው፡፡ ያነበበቸውን ግን ማመን አቃታት፡፡ እንደቅድሙ ህልም እንዲሆን ተመኘች፡፡ በለሆሳስ "አበቃልን" አለች፡፡

-------------------------

"ቃሏን አታከብርም ብለሽ ፈራሽ እንዴ? እንኳን ለሻይ ለኢትዮጵያ ጭቁን ህዝብ የገባሁትን ከባዱን ቃሌን አላጥፍም፡፡ የፈለገው መከራ ቢመጣ፤ ስጋዬን ቆራርጠው ቢጥሉት እንኳን!!" አለች መቅደስ።

ንጹሕም          “....አየሽ አንቺ እማማ ኢትዮጵያ

አየሽ አንቺ እናት ዓለም

ቃል የእምነት ዕዳ ነው እንጂ

የአባት የእናት እኮ አይደለም….” አለች፤ ከፀጋዬ ገብረመድህን ተውኔት ላይ የሰማችውን ቀንጭባ፡፡

--------------------------

"ጓደኛዬ እወድሻለሁ:: ካንቺ በፊት ያድርገኝ" ያለቻት ትዝ አላት:: አንጀቷ ተንሰፈሰፈ....... " መቅደስዬ እኔን ያስቀድመኝ ብዬሽ ነበረኮ! " አለች ዝቅ ባለና የእልህ ሳግ በሚተናነቀው ድምፅ::

"የንጹሕ እንባ ሸሚዙን እያራሰው ነበር:: የእሱ እንባ ደግሞ የንጹሕን በወግ ያልተሰራ ፀጉር እያራሰው ነው:: መቅደስን አያውቃትም ፤ ባያውቃትም ግን ይኸው ታስለቅሰዋለች!!..... እዝራ ለመቅደስ አለቀሰ፤........ በወለሉ ላይ ተጥለው ለሚያያቸው ለጋ ወጣቶች አለቀሰ፤...... ስለወላጆቻቸው አለቀሰ፤......... ስለሚወዳት ኢትዮጵያ አለቀሰ ፤....... ስለመጪው መራራ ጊዜም አለቀሰ.......::" ኢትዮጵያም ስለረገፉትና ሰለሚረግፉት ልጆቿ አለቀሰች:: የኛዋ ኢትዮጵያ እንባዋ አይነጠፍም፤ ልጆቿም የነፃነት ተጋድሏቸውን አያቆሙም:: አባቶቻችን ስለአርበኞቻችን ታሪክ እየነገሩ አሳደጉን:: እኛም ለልጆቻችን ስለሄድንበት የመሰዋአትነት ጉዞ ልንነግራቸው ግድ ይለናል::

---------------------------

... “ታዲያ ለምን ይነካኩኛል? ለምንድነው በቁስሌ ውስጥ እንጨት እየሰደዱ የሚያሰቃዩኝ፣ ለምንድነው የማላሳዝናቸው... ምርር ብላ ማልቀስ ጀመረች። በጉንጮቿ ላይ የሚፈሰው እንባ ከዓይኖቿ ውስጥ የሚመነጭ አይመስልም:: እየተንሰቀሰቀች በእንባዋ ታጠበች። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ጉልበተኛና ኃያል የነበረች ሴት እጅግ ደካማና አሳዛኝ ሆነች። ልጁ ትቷት መሄድ አቃተው።

---------------------------

... እንዳቀፈችው አልጋው ላይ ተመቻችታ ተቀመጠች። ልጁ ዓይኖቹን ገለጥ አድርጎ መልሶ ከደናቸው፤ ትንፋሹ ደግሞ እየቀነሰ የሄደ መሰላት። ፈራች! በጣም ፈራች! “ልጄ ቢሞትብኝስ?” ጥያቄዋ እንደ ኤሌክትሪክ ንዝረት በመላ ሰውነቷ ውስጥ ተሰራጨ፤ የምታደርገው ጨነቃት፤ ዓይኖቿን ከልጁ ላይ ማንሳት አቃታት። ልጁ ትንሿን ሰውነቱን ሲያንጠራራት፤ ደስ አላት። ግን ወዲያውኑ ማልቀስ ጀመረ፤ ተነስታ በጥንቃቄ ወዲያ ወዲህ እያለች አባበለችው፤ በፍጹም ዝም አልል ብሎ ማልቀሱን ቀጠለ።

“ያላረፉ ነፍሶች” ጀምረው ሳይጨርሱ የማያስቀምጡት መጽሐፍ!